Ethiopian
የኢትዮጵያ

AFRICA'S LINK TO THE WORLD

ጥር 19 ቀን፣ 1996 ዓ.ም.

ንቡረ እድ ኤርሚያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ
ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት
የአገልግሎቱ ተጠሪ
የመ.ሣ.ቁ. 812
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ውድ ንቡረ እድ ኤርሚያስ፥

ከሁሉ አስቀድሜ ስለ ብሄራዊ አየር መንገዳችን ካለዎት ፍቅርና የባለቤትነት ስሜት የመነጨ አሁን በሚጠቀመው አርማ ላይ ያለዎትን አስተያየት በማቅረብዎ ላመሰግንዎ እወዳለሁ፡፡

ይህንኑ በተመለከተ ከሕዝብ ግንኙነት ክፍላችን የተሰጠዎት መልስ አጥጋቢ ሆኖ እንዳላገኙት ከደብዳቤዎ ተረድቻለሁ፡፡ሁኔታውን የበለጠ ለማብራራት እንዲረዳ አዲሱን አርማ ይፋ ባደረግንበት ወቅት የተሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ ግልባጭ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዤልዎታለሁ፡፡

ባጭሩ ለማስረዳት ያህል የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባሳለፋቸው 58 ዓመታት የአገልግሎት ዕድሜ በዓርማው ላይ መሠረታዊ ለውጥ አላደረገም፡፡ ከዚህ በፊት በአርማነት ይጠቀምበት የነበረውን የአንበሳ ምስል፥ ባንዲራና ኢትዮጵያዊ ፊደላት አሁንም ይዞ ይገኛል፡፡ ሆኖም ግን የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳድሮ የሚሰራ የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ኢትዮጵያዊ መለያውን ሳይለቅ ዓለም አቀፋዊነትንና ዘመናዊነትን ለማላበስ ጥረት ተደርጓል፡ ለዚህም ከአውሮፕላኑ የኋላ አካል የነበረው የሶስቱ ህብረ-ቀለማት ምልክት ይበልጥ የበረራን አገልግሎት በሚያጐላ መልኩ የላባ ቅርፅ እንዲይዝ ሆኗል፡፡ የዚህም ጭብጥ ተምሳሌነት የተወሰደው ከአዕዋፋት ነው፡፡ "AVIS" በላቲን ቋንቋ ወፍ ማለት ሲሆን የበረራ ኢንዱስትሪውም "አቪዬሽን" የሚለውን ስያሜ ይዟል፡፡ አብራሪዎችም የስራ ማዕረጋቸው በክንፉ ምልክት ይፀድቅላቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድም የወፍን ክንፍ በባንዲራ ቀለም በጭራው ላይ አስውቦ ሲያበር መቆየቱ ይህንን መሠረት ያደረገ

ነው፡፡ በመሆኑም የወፍ ክንፍ ለበረራ ምሳሌነቱ ተገቢ ነው፡፡ አያሌ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ኩባንያዎችም በተለያየ መልኩ በአርማቸው ላይ ያውሉታል፡፡

ከዚህ ባሻገር የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመላ ኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ንብረት እንጂ የአንድን ብሔር፥ ሃይማኖት፥ ወይም የፖለቲካ ቡድን ማንነትና ፍላጐት የሚያንፀባርቅ አለመሆኑን እየገለፅኩ፣ የመላ ኢትዮጵያ መታወቂያ የሆነውን ሰንደቅ አላማ ጉልህ በሆነ መልኩ ድሮም፣ አሁንም በአውሮኘላኖቹም ሆነ በሌሎች ንብረቶቹ ላይ የሚንፀባረቅ መሆኑን ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡

አዲስ ከገዛናቸው አውሮፕላኖች መካከል የመጀመሪያው B-767-300ER ህዳር 16 ቀን 1996 ዓ.ም. አዲስ አበባ ሲገባ ከተነሳቸው ፎቶግራፎች መካከል አንዱን የምልክልዎት አንበሳው ከሌላው የአውሮፕላን ገፅታ ጋር በማይጋጭ መልኩ አሁንም በፊተኛው የአውሮፕላኑ አካል ላይ እንዳለ ለማስረዳት ነው ፡፡

ለማጠቃለል፥ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አርማ፥ አየር መንገዱ የኢትዮጵያዊነት ግርማውን ሳይለቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተፎካካሪነትና በብቃት እያደገና እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አገልግሎቱንም ከሌሎች አየር መንገዶች የላቀ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ደንበኞቻችን ለምን መልኩ ተቀየረ ብለው የሚሸሹት ሳይሆን ተራማጅ (modern) በሆነውና ብቃት ባለው አገልግሎቱ ረክተው ሁልጊዜም የሚመርጡት፥ ክብሩንና ሞገሱን የሚመሰክሩለት አየር መንገድ እንደሚሆን ያለንን ታላቅ እምነት እገልፃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ማክዳ ዮሐንስ
የማስታወቂያ ማስፋፊያና
የደንበኞች አገልግሎት ዋና ክፍል ኃላፊ

# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።

## Ethiopia: The Kingdom of God Services

ጥቅምት ፲፯ ቀን፥ ፲፱፻፺፯ ዓ. ም.

ይድረስ፡- ለአቶ ብሥራት ንጋቱ፤
የኢትዮጵያ አየር መንገድ፡ ዋና ሥራ አስኪያጅ፤
መልእ. ሣ.ቁ. ፲፯-፺፩፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።

<u>ጉዳዩ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ መታወቂያ ምልክት ስለመለወጡ።</u>

በቅድሚያ፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ስም አቀርብልዎታለሁ።

በአሜሪካ የሚገኙ፡ እውነተኞች ኢትዮጵያውያንን ለማገልገል፡ የሰሙኑ ሕማማትንና የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ፡ በቅርቡ፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ጥያራ፡ ወደዋሽንግተን ዲ. ሲ. ተጉዤ፡ በዚያ ሣለሁ፡ የአየር መንገድዎን፡ የኀዋው አውታር ሰሌዳ፡ ከመቀመሪያዬ ከፍቼ ስመለከት፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ መታወቂያ ኾኖ የኖረው፡ የ"አንበሳው" ምልክት (Logo) የተለወጠና በአዲስ የ"ላባ" ምልክት የተተካ መኾኑን አየሁ። እኔም፡ ይህ የኾነበትን፡ እርግጡን ምክንያት ለማወቅ፡ በፈረንጆቹ አቈጣጠር፡ በ10/3/03፡ የሕዝብ ግንኙነት ክፍልዎን፡ በዚያው የኀዋ አድራሻው፡ በእለቄጥሩ-ደብዳቤ (e-mail) ጠይቄ፡ ያገኘሁት ምላሽ፡ በቂ ባለመኾኑ፡ የተሟላ መልስ እንዲሰጠኝ እንደገና በ10/6/03 ጻፍሁለት፤ ነገር ግን፡ ይህን ደብዳቤ እስከጻፍሁበት፡ እስከዚህ ቀን ድረስ፡ ከዝምታ በስተቀር፡ አንዳችም ውጤትን ስላላገኘሁ፡ ከዚሁ ክፍልዎ ጋር፡ በኀዋው አውታር የተለዋወጥኋቸውን፡ እነዚሁኑ መልእክቶች ቅጂያቸውን፡ ከዚህ ጋር አያይዤ በማቅረብ፡ ይህን ደብዳቤ፡ በቀጥታ ለእርስዎ እንድጽፍ ተገድጃለሁ።

መገደዴም፡ በኢትዮጵያዊነቴ ብቻ አይደለም፤ አየር መንገዱ፡ ከትምህርት ዓለም ከወጣሁ በኋላ፡ የዛሬ አርባ ስድስት ዓመት፡ ሥራ የጀመርሁበት ድርጅት በመኾኑም ጭምር ነው፤ ከዚህም በላይ፡ ከልጅነት ዕድሜዬ አንሥቶ፡ የኢትዮጵያ የኾነው መልካሙ ሕያው ቅርስ ኹሉ እንዲጠበቅ፡ በሚደረገው በማናቸውም ተግባር ውስጥ፡ ከቤተሰቤና ከሚመስሉኝ ጋር ኾኜ፡ የበኩሌን አስተዋጽዖ ለማበርከት፡ ቃል ኪዳን የገባሁ በመኾኑም ነው። ይህን አቋሜንም፡ በዚህ ደብዳቤ አናት ላይ የሠፈረው፡ የተሠማራሁበት የአገልግሎት ስያሜ፡ ራሱ፡ በግልጽ ያመለክትዎታል። ከዚህ ጋር፡ ለአየር መንገዱ ቤተ መጻሕፍት ለምንባብ ይጠቅሙ ዘንድ በማሰብ፡ በጥቅምት ፯ ቀን፥ ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. በተጻፈ ደብዳቤዬ አማካይነት፡ በስምዎና በኃላፊነትዎ የላክኋቸውን፡ *ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!፥ ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፍረጃ!* እና Ethiopia: The Classic Case የተባሉትን ሦስት መጻሕፍቴን ተመልክተዋቸው ከኾነ፡ ይህንኑ የአባባሌን እውነታ፡ ከእነርሱ ሊረዱና ሊያረጋግጡ እንደቻሉ እገምታለሁ።

...፪

መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፤ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭፤ ፳-00-፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org

የሕዝብ ግንኙነት ክፍልዎ ሊሰጠኝ ያልፈለገውን: ወይም ያልቻለውን ምላሽ: ከእርስዎ እንደማገኝ÷ እርስዎም: ፈቃድዎ ኾኖ: እንደሚሰጡኝ በማመን የማቀርብልዎ አጠቃላይ ጥያቄ: *<u>"የኢትዮጵያ አየር መንገድ: ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ: መታወቂያ ምልክቱ ኾኖ እስከዛሬ የኖረው የአንበሳው ምስል: ለምን በአዲሱ የላባ ምልክት ተለወጠ?"</u>* የሚል ነው:: ይህን ጥያቄ መሠረት በማድረግ: ከዚህ በሚከተሉት ተዛማጅ ትችቶችና አስተያየቶች እንዳፍታታው ይፍቀዱልኝ!

በመሠረቱ: የቀደመው: የአንበሳው ምልክት እንዲለወጥ÷ በአዲሱ ላባም እንዲተካ ለምን አስፈለገ? የአንበሳው ምልክት መኖር: ከመጥቀም በቀር: ከቶ ምን ጉዳት አድርሶ ነው: ጨርሶ እንዲወገድ: ይህን የመሰለው ውሳኔ ሊሰጥበት የበቃው? ያውም: "ኢትዮጵያውያን ነን!" በሚሉ: በራሱ ወገኖች÷ በራሱ አገርና በራሱ ንብረት ላይ? ከአንበሳው ጋር: ላባው ቀድሞም እንደነበረ÷ ለማናቸውም በራሪ: የተለመደ ምልክት ኾኖ እንደሚሠራም ይታወቃል፤ ታዲያ: በምልክትነቱም ኾነ: በተፈጥሮ ባሕርዩ: ከላባውና ከአንበሳው ማንኛቸው: "ይበልጣል!" ተብሎ ነው: አንበሳው ቀርቶ: ላባው የተመረጠው? ላባ ደግሞ: ከብዙ አእዋፋት ክንፎች የሚገኝ ነው፤ የርግብም÷ የንስርም÷ የዶሮም÷ የቍራም÷ የጭልፊትም ላባ አለ? የየትኛው ነው ሊባል ነው? ከኾነ ደግሞ: ግልጽ እንደኾነው እንደአንበሳው ምስል: ለምን: የዚያ የባለክንፉ ወፍ ምስል: በሙሉ አካሉ ተሥሎ እንዲታይ አልተደረገም?

ውሳኔውንና ድርጊቱን: በማስተዋል ሲመለከቱት: ያስደንቃል! ለምልክትነት÷ ያውም ለኢትዮጵያ አየር መንገድ: ከአንበሳ የሚበልጥ: ሌላ ምን ዓይነት "የተሻለ ምልክት ሊኖር ይችላል!" ተብሎ ነው: ይህን የመሰለው ዕቅድ: ቀድሞውንም ቢኾን: እንዲህ: ሊወጠን የተቃጣው? ከዚያም አልፎ: በመጨረሻ: ያ: ጸንቶ ሲሠራበት የቆየው ምልክት ተወግዶ: በሌላ እንዲተካ ለማድረግ የተደፈረው? አየር መንገዱ: በመላው ዓለም: በገናናነት የታወቀበት ይህ: የኖረው የአንበሳው ምልክት እንዲቀርና በአዲስ እንዲቀየር ሲደረግ እኮ: ድርጅቱንና አገልግሎቱን: በመላው ዓለም ለማስተዋወቅ: ለስድሳ ዓመታት ያህል የፈሰሰው: ያ ኹሉ የእውነተኞች ኢትዮጵያውያን ጉልበትና እውቀት÷ ሙያና ብልሃት÷ ሀብትና ሕይወት ጭምር: በከንቱ ባከነ ማለት አይደለምን? ለሀገር ፍቅር÷ ለነጻነት ክብርና ለወገን ቤዛነት ተብሎ: ለጥቂት ጊዜ: በጦር ሜዳ ላይ: በግዙፍ መሣሪያ: ከሚካኼደው የትጥቅ ትግልና ከሚከፈለው የደም ዋጋ ይልቅ: በሰላሙ ጊዜ: ለረዥም ዓመታት: ሳይቋረጥ የሚቀርበው መሥዋዕትነት: የሚበልጥበት ጊዜም እኮ እንዳለ መገንዘብ ይገባል! የቀደሙትና የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት: ይህን የአንበሳውን ምልክት ይዞ ለኖረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ: እስካሁን የከፈሉትን: ይህን የመሰለውን መሥዋዕትነት: ዛሬ: በየደረጃው ያላችሁት ባለሥልጣኖች ኹሉ: እንዴት ሳታጤኑት እንደቀራችሁ ይገርመኛል:: በአየር መንገዱ የአንበሳው ምልክት ላይ የጣላችሁትና ልታስፈጽሙ የምትሞክሩት: ይህ ውሳኔያችሁ: በቀጥታ: ይህን እውነታና ፍትሕ ያዛነፈ መኾኑን ልታውቁት÷ ሌላውም: የሚመለከተው ኢትዮጵያዊ ኹሉ ሊያውቀው ይገባል ይመስለኛል::

በዚህ ውሳኔያችሁና ድርጊታችሁ: የቀረው ዓለም ብቻ ሳይኾን: በይበልጥ: የቅርቦቹ: አፍሪቃውያን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ጭምር: እኛን ኢትዮጵያውያንን: በምን ዓይነቱ የግምትና የትዝብት ሚዛን ላይ እንዳስቀመጡን ለማወቅ: ብዙም: የጥናት÷ ወይም የምርምር÷ ወይም የጥያቄ መሥፈርትን ማቅረብ ከቶ የሚያስፈልግ አይኾንም፤ በቀላሉና በገሃድ ሊያውቁን እንደቻሉ አያጠራጥርምና:: ኢትዮጵያዊው አንበሳ እኮ: የኢትዮጵያም÷ የአፍሪቃም ብቻ አይደለም፤ የዓለሙ ኹሉ እኮ ነው! አንበሳ: እንደማናቸውም ሕይወት ያለው ፍጡር: አንድ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ነው:: ስለዚህ: የአንበሳው ምልክት: ለኢትዮጵያና ለአፍሪቃ ብቻ ሳይኾን: ለዓለሙም ኅብረተሰብ ሳይቀር: የልበ ሙሉነትና የቻይነት÷ የትእግሥትና የአሸናፊነት÷ የቀዳሚነትና የበላይነትም ምልክት ነው!

...፫

ታዲያ፡ ይህን የመሰለውን በጎ ምልክት ከማስወገድ ያደረሰ፡ ምን ጉዳኛ ምሥጢር ተገኘ? በአፍሪቃ ክፍለ ዓለም፡ ቀዳሚነትን፥ አስተማማኝነትንና ዝናን ላተረፈው፡ ለኢትዮጵያ አየር መንገድስ፡ ከአንበሳው የተሻለና የበለጠ፡ ሌላ ምን ምልክት "አለ!" ተብሎ ነው፡ መተኪያ የተፈለገለት? አንበሳውስ፡ ለማን ሊኾን ነው? ማንስ ሊወስደው ነው?

ይህን የተወደደውን፥ የተከበረውንና የገነነውን የአንበሳውን ምልክት፡ ዛሬ፡ እኛ ከተውነው እኮ፡ ነገ፡ አንድ ሌላ የአፍሪቃ፥ ወይም፡ የዓለም-አቀፍ አየር መንገድ፡ የንግድ ምልክቱ አድርጎ ሊጠቀምበት አይደለምን? ይህ፡ እንዴት ሳያሳስባችሁና ሳያሳዝናችሁ ቀረ?! በዚህ ረገድ፡ የተስማማችሁበት ውሳኔና አድራጎታችሁ፡ የኢትዮጵያ የኾነውን መልካም ጥሪት፥ ቅርስና ውርስ ኹሉ፡ በልዩ ልዩ ስልት፡ ቀስ እያሉ ለማጥፋት፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ጠላቶች የተነደፈው የቆየው ምሥጢራዊ ዕቅድ፡ በገሃድ መጀመሩን ማወጅ መኾኑን እንደሚጠቁም፡ ለማንም አስተዋይ ተመልካች ግልጽ ነው።

ኢትዮጵያ፡ የአፍሪቃ የዱር አራዊትና እንስሳት ሀብት ምንጭና ማኅደር ስለኾነች፡ "አንበሳ"፡ የዚያም ይዞታችን ምልክት ነው። ከዚህ የተነሣ፡ ለአገር ጐብኚዎችም፡ ጥሩ መስሕብ ኾኖ ኖርዋል። ይልቁንም፡ አንበሳው፡ በዓለም ላይ ከሚኖሩት ሕዝቦች ኹሉ ይልቅ፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን፡ የተለየ አግባብነት አለው። የአኵስም ሓውልት፡ ከባዕዱ አደባባይ ወደጥንታዊ ቦታው ይመለሳል ተብሎ በሚጠበቅበት በአሁኑ ወቅት፡ እነዘርዓይ ድረስ የተሠዉለት የአንበሳው ምልክት፡ በአገሩ ላይና በአገሩ ልጆች፥ ከአገሩ መቀመጫ እንዲወገድ የመደረጉ ነገር፡ አዎን፡ በእርግጥ፡ ግራ የሚያጋባና የማይጣጣም ኹነታ ብቻ ሳይኾን፡ አያሌ ትዝታዎችን ጭምር ስለሚቀሰቅስ፡ አግባብነት አለው። ይኸውም፡ መጽሐፍ ቅዱስን ከተቀበለው ከዓለም ሕዝብ ኹሉ በፊት፡ ቅድሚያውን በመውሰድ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ለማንነቱ መታወቂያና ለመንግሥቱ ምንነት መለያ እንዲኾነው የመረጠው፡ ድል አድራጊውን የመጽሐፍ ቅዱሱን አንበሳ በመኾኑ ነው። የዚህ ምልክት ባለቤት መኾን ደግሞ፡ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን፡ ማንም ላላገኘው፥ ለአያሌ ሺህ ዘመናት ለኖረው፡ ዘለዓለማዊ ለኾነው የነጻነት ህልውናቸው፡ ባለመብትነቱን፡ በሚያስተማምን ኹኔታ አረጋግጦ አስጨብጧቸዋል።

"አንበሳ"፡ ከኹሉም በላይ፡ ዓለምን ላዳነው፡ ለእግዚአብሔር ልጅ እንኳ ሳይቀር፡ ምሳሌ ሊኾን የተመረጠ ምልክት መኾኑን፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ማስረዳት አስፈላጊ አይመስለኝም፤ *"የማርያም መቀነት"* በተባለው ሰንደቅ ዓላማቸው ማዕከል ላይ ሠፍሮ፡ የአገራቸው፥ የሕዝብነታቸውና የመንግሥታቸው መለያነቱንና መታወቂያነቱን፡ ለዓለሙ ኹሉ ሲያረጋግጥ የኖረ መኾኑን፡ ማንም ሊያስተባብለው ከቶ አይቻለውም፤ ምክንያቱም፡ *"ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!"* ማለትም፡ *"ከይሁዳ ነገድ የተገኘው አንበሳ፡ ድል አደረገ!"* የሚለውን፡ ዓለም የተቀበለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሊበቁ ካልቻሉትና ካልፈለጉት ከእስራኤል ወስዶ፥ *"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"* ማለትም፡ *"እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!"* ወደተባለችው ወደ *"ኢትዮጵያ"* አምጥቶ፡ በኢትዮጵያዊነቱ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ የዘለዓለም ውርስ ስላደረገው ነው።

የአንበሳው ምስል፡ ለፍጡራን፥ በተለይም ለኢትዮጵያውያን፡ የደኅንነት ጥበቃና የዋስትና ምልክት መኾኑንም ማንም ሊያስተሓቅረው የሚችል ያለ አይመስለኝም፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከተቋቋመ ጀምሮ፡ ስንት የበረራ አደጋዎች ደረሱበት? ከእነዚያ አደጋዎች የተነሣስ፡ ስንት ሰዎች፡ የመቍሰል፥ የአካል ጉዳት እና/ወይም የሞት አደጋ አገኛቸው? ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር፡ ምንም ያህል አደጋ እንዳልገጠመው የሚቈጠር መኾኑ እርግጥ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ፡ በዓለም የአየር ተጓዦችና የአገር ጐብኚዎች ዘንድ፡ በስመጥርነት ከታወቀባቸውና ከተመዘገበባቸው መልካካም ባሕርያቱ መካከል፡ ዋነኛና ቀዳሚ ኾኖ የሚጠቀሰው፡ ይኸው የደኅንነቱ ዋስትና መኾኑ ተዘውትሮ ይነገራል።

የዚህ ምክንያት፡ በሰዎች ጥበብና ኃይል ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ሰንደቅ ዓላማችን ምሳሌዋ የኾነው፡ የእናት ኢትዮጵያና "አንበሳው" ምሳሌው የኾነው፡ የኢትዮጵያ አምላክ ጥበቃ መኾኑን፡ እኛ ኢትዮጵያውያን እንደምናምን፡ ዛሬ፡ በአየር መንገዱ አመራር ላይ ለምትገኙ ባለሥልጣኖች ማሳወቅ አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ። ለዚህም፡ ቀደም ብሎ፡ በሱዳን በረሃ ተሰናክሎ፡ ያለምንም ጉዳት፡ በተአምር ያረፈውን Constellation (ኮንስተሌሽን) የተባለውን፡ ባለአራት ውልብልቢት ጥያራና በቅርቡ፡ ከአሸባሪዎች የጠለፋ ወንጀል የተነሣ፡ በነዳጅ ማለቅ ምክንያት፡ በምሥራቅ አፍሪቃ ባሕር ላይ ለማረፍ ተገድዶ፡ አያሌ መንገደኞች፡ በተአምር፡ ከሞት የዳኑበትን፡ ገሞራዊውን (Jet) ጥያራ፡ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። የኢትዮጵያዊው አንበሳ የአደጋ ጠባቂነቱ ዋስትናና ተአምራዊነት፡ በገሃድ የታየበት ሌላው ምስክር ደግሞ፡ ዋና መሥሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ ኾኖ፡ በመላዋ የኢትዮጵያ ምድር፡ መላውን ሕዝባን፡ ከዓቅሙ በላይ በማገልገል ላይ ያለው፡ "አንበሳ" በሚል ስም፡ ሥዕሉን አንግቦ የሚታወቀው፡ የሕዝብ ማጓጓዢያ ነው፤ ይህ ድርጅት፡ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ፡ ለረዥም ዘመን፡ በተሽከርካሪዎቹና በመንገደኞቹ ላይ የደረሰበት አደጋ፡ እንደአየር መንገዱ ኹሉ፡ የአነስተኛነቱ መጠን፡ ለዚህ እውነታ ተጨማሪ ማረጋገጫ ስለኾነ፡ እዚህ ላይ፡ እርሱንም በምሳሌነት እንድጠቅሰው ተገድጃለሁ።

የአንበሳው ምልክት፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ፡ ራሱን የቻለ፡ በቂ የህልውና፥ የባህልና የታሪክ፥ የሃይማኖትም መሠረትነት ያለው፥ በዚህም እየተመሰከረለት የኖረ መኾኑ እየታወቀ፡ ይህን የመሰለውን ውሳኔ ወስኖ በተግባር ላይ ለማዋል መጣደፍ፡ ከአገርና ከወገን ፍቅር ተራቍቶ፡ የራስን ማንነት እንደመካድ የሚያስቈጥር መኾኑ፡ ከአስተዋይ ተመልካቾች የሚሠወር አይደለም። የዚህም እውነታ፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ጠላቶችና ወደረኞች፥ ተቀናቃኞችና ባላጋራዎች፡ የእየራሳቸውን አገር፡ የአየር መንገዶች፡ በየባህላቸውና በየሃይማኖታቸው ምልክቶች ሳይቀር እንዲታወቁና እንዲያሸበርቁ እያደረጉ ሲሠሩ፡ የኢትዮጵያው አየር መንገድ ግን፡ ይህን ገናና ምልክቱን እንዲያጣ፡ ሲያሴሩና ሲጥሩ የኖሩትን ክፉ ዓላማቸውን፡ ዛሬ፡ በአጋጣሚው በመጠቀም፡ ከግብ ለማድረስ ቆርጠው በተነሣሡበት ጊዜ፡ እነርሱን ለማስደሰት ሲባል፡ የተፈጸመ መስሎ፡ እነሆ በገሃድ ይታያል። ይህን ለማለት ያስደፈረኝ፡ በቅርቡ፡ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ምሉክ፡ ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ፡ ለጕብኝት፡ በዋሽንግተን ዲ. ሲ. ከተማ ተገኝተው በነበረ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ጽሕፈትቤት ውስጥ ተጠርቶ በነበረው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ፡ ስለዚሁ የአንበሳው ምልክት መወገድ፡ ከኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት ውጪ ከኾነ አንድ ግለሰብ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡትን መልስ፡ በነፋስ ሥዕል ቀርቦ ያየሁና የሰማሁ በመኾኔ ነው።

ኢትዮጵያውያን፡ በታወቀው የስደተኞች መልካም አቀባበላቸውና በጎ መስተንግዷቸው፡ ከጥንት ጀምረው ባደረጉላቸው ቸርነት ምክንያት፡ በኢትዮጵያ ደልቷቸውና ተመችቷቸው በሚኖሩ፡ የሃይማኖት ወገኖች ዘንድ፡ በጠቅላላ የአንበሳው ምልክት ጥላቻ መኖሩ ወይም ፀረ አንበሳ አቋም ያለ መኾኑ፡ በዚያ ግለሰብ ጥያቄ፡ በገሃድ ገዝፎ ይታይ እንደነበረ፡ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ የነበረውና ትርኢቱን የተመለከተው ኹሉ ያስታውሰዋል። ከዚህ የተነሣ፡ ይህ፡ ዛሬ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ላይ ጸንቶ የኖረው፡ የአንበሳው ምልክት እንዲወገድ፡ የተበየነው ውሳኔና ውሳኔውን በሥራ ላይ ለማዋል የተፈጸመው ድርጊት፡ በአየር መንገዱ ብቻ ተወስኖ የሚቆም ሳይኾን፡ በአዲስ አበባና በሌሎቹ ከተሞች፥ ባጠቃላይም፡ በመላዋ የኢትዮጵያ ምድር ላይ ያሉት፡ የአንበሳው ሥዕሎች፥ ምስሎችና ሓውልቶች፥ በጥበቃ ያሉትንና በዱር የሚኖሩትን ሕያዋን ተንቀሳቃሽ አንበሶችን ሳይቀር ለማጥፋት፡ የተጀመረው ዘመቻ፡ መቀጠሉም የማይቀር መኾኑን፡ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ፡ ከጥርጣሬ በላይ፡ አውቆትና ነቅቶበት እንዲጠባበቅ ወደሚያደርገው ደረጃ አድርሶታል።

...፯

ለነገሩማ፡ የኢትዮጵያ ጠላቶች አሲረውበት የነበረውን ምሥጢራዊዉን ዕቅድ፡ ምልክቱ የኾነው፡ የድል አድራጊው አንበሳ ኃይል አክሽፎለት፡ የመፍረሱ ክፉ ዕድል፡ ተሰነካክሎ ቀረለት እንጂ፡ ይኸው ኢትዮጵያዊው አየር መንገድ፡ ከእናት አገርዋ፡ እንድትገነጠል ላደረጓት የኤርትራ መሪዎች እንዲሸጥ፡ ውሳኔ ተሰጥቶበት የነበረ ሙከራ መኖሩ ይረሳልን? አይረሳም:: ከዚህም በላይ፡ "ደርግ" የተባለው፡ የከሃዲዎችና የዓመፀኞች መንግሥት ተነሥቶ፡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልበውን፡ የድል አድራጊውን አንበሳ ምልክት በሻረ ጊዜ፡ በዚህ እጅግ ከባድ በኾነው የአመንዝራነት ኃጢኣት፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብና ቤተ ምልክና ብቻ ሳይኾኑ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ጭምር፡ በግብረ አበርነት ተባብረውበት፡ ይኸው ኹኔታ፡ እነሆ፡ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ ቀጥሎ የለምን? ጉዳዩን፡ በዚህ አኳያ ሲመለከቱት፡ ዛሬ፡ የአንበሳውን ምልክት ለማስወገድ፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ባለሥልጣኖች የተፈጸመው ድርጊት፡ እምብዛም ላያስደንቅ ይቻል ይኾናል፤ ያ ቀዳሚው ታላቅ በደል፡ ለዚህኛው ጥፋት፡ መንሥዔና ማበረታቻ ምክንያት ሳይኾን እንዳልቀረም ይታመናልና::

የአየር መንገዱ ባለሥልጣኖች፡ የአንበሳውን ምስል ለማስወገድ፡ ቆርጠው የተነሣሡት፡ ምልክቱ፡ ኢትዮጵያዊ ከመኾኑ የተነሣ፡ የሚጠሉትን ወገኖች ለማስደሰት ብቻ ሳይኾን፡ ከእነርሱ የሚያተርፈውን፡ የንግዱንና የገንዘብ ገቢውን መጠን ጭምር፡ ከፍ አድርጎ ለማሳደግ አስበው ከኾነም፡ የአገርና የማንነት መታወቂያ የኾነው ሕያው ውርስ፡ በዚህ መልክ፡ ለዚህ ጊዜያዊ ለኾነው ጥቅም ተብሎ መለወጡ፡ እጅግ ያሳዝናል፤ ያሳፍራልም::

እንግዴህ፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ በዓለሙ ኅብረተሰብ ዘንድ፡ ታውቀውበትና ተከብረውበት የኖሩትን፥ ከፍተኛ መሥዋዕትነትም ከፍለው ያቋቋሙትና የደከሙበት፡ ዛሬ፡ እርስዎ የሚመሩት፡ ይህ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ገንኖ የኖረበትን፡ እንዲህ ያለውን፡ ታላቅና ከባድ ቅርስ ነው፡ የዛሬው ትውልዳቸው፡ በአሳፋሪ ኹኔታ፡ በታናሽና በቀላል ምልክት ሊተካ እየሞከረ ያለው::

ስለዚህ፡ ከላይ፡ ያሠፈርሁትን ሓተታ፡ በኢትዮጵያዊነት ቅን ልቦናና እውነተኛ ሕሊና ተመልክተውና አመዛዝነው:-

፩ኛ፡ ለሕዝብ ግንኙነት ክፍልዎ፡ ቀደም ብዬ ላቀረብሁት ጥያቄ፡ ተገቢው ግልጽ መልስ ተብራርቶ ሊሰጠኝ ሲገባ፡ ያ የሥራ ክፍል፡ ይህን ግዳጅ ሊፈጽም ያልቻለው ለምን እንደኾነ፥ ምናልባት፡ ከጥያቄው ከባድነት የተነሣ ከኾነም፡ ይህንኑ ምክንያት፥ ወይም ትክክለኛውን መልስ፡ በእርስዎ በኩል እንዳገኝ ያደርጉልኝ ዘንድ፡ በትሕትና እጠይቃለሁ፤

፪ኛ፡ ከላይ በ፩ኛው ተራ ቍጥር የቀረበው ጥያቄ፡ ተመለሰም፡ አልተመለሰም፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ መለዮና መታወቂያ የኾነው፡ የአንበሳው ምልክት፡ የኢትዮጵያ ሀብትና የሕዝቧ ሕያው ውርስ ስለኾነ፡ ከነበረበት ቦታው ሳይነሣና ክብሩ ሳይነካ፡ ባለበት ሊጸና ስለሚገባ፡ ምልክትነቱን፡ በላባ ለመለወጥ የተደረገው ውሳኔ፡ ተሽሮ፡ ይኸው የአንበሳው ምልክት፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓርማነቱ እንዲቀጥል ያደርጉ ዘንድ በአክብሮት አሳስባለሁ::

፫ኛ፡ "ምናልባት፡ ጉዳዩ ተጣርቶ፡ ለሕዝብ መገለጽና መታወቅ ይኖርበታል!" የሚያሰኝ ምክንያት ቢገኝ እንኳ፡ የዚህ አስተሳሰብ ውጤት እስኪገኝ ድረስ፡ የአንበሳውን ምልክትነት፡ በላባ የለወጠው ውሳኔ፡ በሙሉ ታግዶ፥ ማለትም፡ የአንበሳው ምልክት፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓርማነቱ መቀጠሉ እንደተጠበቀ ኾኖ፡ ይህ ያቀረብሁልዎ አቤቱታ፡ በሙሉ ተፈጻሚ እስኪኾንና ፈቃድዎ ኾኖ፡ ውጤቱን፡ በጽሑፍ እስኪያስታውቁኝ ድረስ፡ እኔና እኔን የመሰሉት ኹሉ፡ እርስዎ፡ በኃላፊነት በሚመሩት፡ በዚሁ አየር መንገድዎ፡ ከአሁን ጀምሮ፡ ከመገልገል፡ ራሳችንን ያገለልን መኾናችንን ሳሳውቅዎ፡ በትካዜ ነው::

ከዚህ ውሳኔ የደረስነውም: ምንም እንኳ: በገንዘብ ይዞታችን በኩል ያለው: የእኛ ዓቅም: የአንበሳው ምልክት እንዲወገድ ባደረገው ውሳኔያችሁ ከሚደሰቱት: ከሌሎቹ ባዕዳን ወደረኞቻችን ጋር ሲነጻጸር: በአየር መንገዱ ዘንድ: ከግምት ውስጥ ሊገባ የማይችል: ኢምንት ኾኖ እንደሚታይ ብናውቅም: ይኸው ድርጅትዎ: ታውቆበትና ተከብሮበት የኖረውን÷ *"ኢትዮጵያዊ መልኩ"* የኾነውን: የአንበሳውን ምልክት: ያለበቂ ምክንያት እንዲለውጥ በመደረጉ: በእኛ በኩል: ኢትዮጵያዊዉን የእምነት አቋማችንን: መሠረት በማድረግ: ልንፈጽመው የሚገባን ግዳጅ: ለጊዜው: ከዚህ የማያልፍ መኾኑን ባለመዘንጋታችን መኾኑን እንዲገነዘቡት እወድዳለሁ:: ይህም: ኢትዮጵያዊ የኾነው ነገር ኹሉ: መልኩን ሊለውጥ እንደማይችል: *"ኢትዮጵያዊ መልኩን÷ ነብርም ዝንጕርጕርነቱን ሊለውጥ ይችላልን?"* ተብሎ: በታላቁ መጽሐፍ የተነገረለት ሕያው ቃል: ብርቱ ጥንቃቄ ተደርጎበት ሊጠበቅ እንጂ: በማቃለል ሊታይ እንደማይገባ: አበክሮ ያሳስባል::

ይህ ውሳኔያችን በሥራ ላይ መዋል መጀመሩን: ቅጂውን: ከዚህ ጋር አባሪ አድርጌ የላክሁልዎ: እኔ: በቅርቡ: ከአዲስ አበባ: ወደዋሽንግተን ዲ. ሲ. ተጕዤበት በነበረው: የኢትዮጵያ አየር መንገድ የደርሶ መልስ የመብረሪያ ወረቀት: መጠቀምን ትቼ: ወደአዲስ አበባ ለመመለስ: ተመዝግቤበትና ይዤው የነበረውን ቦታ: የሠረዝሁ መኾኔን የሚያሳየው: ለኒው ዮርኩ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤትዎ የጻፍሁት ማስታወሻ ያረጋግጥልዎታል::

የዚህን: ለእርስዎ የጻፍሁትን የዋናውን ደብዳቤ ግልባጭ: ጉዳዩ: ለሚመለከታቸውና አግባብ ላላቸው ኹሉ: ያስተላለፍሁ መኾኔን እያሳወቅሁዎ: ቅን መልስዎን: በተስፋ እጠባበቃለሁ::

ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ (ንቡረ እድ)
የአገልግሎቱ ተጠሪ

ግልባጭ:-

ለክቡር የመቶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ፤
የኢትዮጵያ ርእሰ ብሔር፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ::

ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ፤
የኢትዮጵያ ቤተ ምልክና ጠቅላይ ምሉክ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ::

ለብፁዕ አባ ጳውሎስ፤
የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት እጨጌ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ::

ለክቡር አቶ ዳዊት ዮሓንስ፤
የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ አፈ ጉባዔ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ::

ለክቡር አቶ ሥዩም መስፍን፤
የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ምሉክና
የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባለአደራ ምርፋቅ ሊቀ መንበር፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ::

ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች ማኅበር፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።

ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት፤
ኒው ዮርክ፤ ኒው ዮርክ፤ ዩ. ኤስ. አሜሪካ።

ለኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ጽሕፈት ቤት፤
ዋሽንግተን፡ ዲ. ሲ.፤ ዩ. ኤስ. አሜሪካ።

ለአንበሳ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅት፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።

ለአንበሳ የሕዝብ ማመላለሻ ድርጅት ሠራተኞች ማኅበር፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።

ለሚመለከታቸው ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ኹሉ፤
በያሉበት።